የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፳፱
አዲስ አበባ የካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4[th] Year No. 29
ADDIS ABABA - 5[th] March, 1998

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፭/፲፱፻፺ ዓ.ም.
ለመንገዶች ልማት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ከዓለምአቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ...... ገጽ ፯፻፳

## CONTENTS

Proclamation No.105/1998
International Development Association Credit Agreement for Financing the Road Sector Development Program Ratification Proclamation ...... Page 720

### አዋጅ ቁጥር ፩፻፭/፲፱፻፺
### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለመንገዶች ልማት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ.ዲ.አር ፪፻፳፬ ሚሊዮን ፭፻ሺህ (ሁለት መቶ ሃያ አራት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፰ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመ በመሆኑ፣

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፣

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለመንገዶች ልማት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፭/፲፱፻፺"ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### PROCLAMATION NO. 105/1998
### A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

WHEREAS, a Development Credit Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit amount of two hundred twenty four million five hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 224,500,000) for financing the Road Sector Development Program, was signed in Washington D.C, on the 25[th] day of January, 1998;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Credit Agreement at its session held on the 5[th] day of March, 1998;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the ''International Development Association Credit Agreement for Financing the Road Sector Development Program Ratification Proclamation No. 105/1998.''

፪. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፰ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመው ቁጥር ፫ሺ፴፪ ኢ.ቲ. የብድር ስምምነት ነው።

፫. <u>የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ኤስ.ዲ.አር. ፪፻፳፬ ሚሊዮን ፭፻ ሺህ (ሁለት መቶ ሃያ አራት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት



2. *Definition*

In this Proclamation "Credit Agreement" means the Credit Agreement No. 3032 ET signed in Washington D.C., on the 25th day of January, 1998 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of two hundred twenty four million five hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 224,500,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 5th day of March, 1998.

Done at Addis Ababa, this 5th day of March, 1998.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ድርጅት
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE